SWEDISH
Extraordinary care. Extraordinary caring.℠

# የውልደት አማራጮች የተጠቃሚ መምርያ

# Birth Preferences User’s Guide (Amharic)

ይህ መምርያ የእርስዎን የውልደት አማራጮች ቅጽ እንዲሞሉ ለመርዳት የታለመ ነው። ይህንን ቅጽ እንዲሁም ከእንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር በቅድመ ወሊድ ክትትል ቀጠሮችዎ ባንዱ ቀን ፣እንዲሁም ስለዚያ ያሎትን ማንኛውንም ጥያቄዎችን ወይም ስለዚህ መምርያ እንዲወያዩ እንመክርዎታለን።

**ስለኔ/እኛ፣** ይህንን ክፍል ለእንክብካቤ ቡድንዎ ስለራስዎ የተወሰነ ነገር ለመንገር እንደ ይህ ይህ የመጀመርያ ልጅዎ መሆኑን ወይም ሌላ ልጆች ያልዎት መሆኑን፣ የሚሰሩትን የስራ አይነት፣ በዚህ እርግዝና ላይ ያሎት የኋላ ታሪክ፣ የሚዝናኑበት የጊዜ ማሳለፍያ፣ ወዘተ።

**የምጥ የድጋፍ ቡድን (ስሞች እና ግንኙነቶች)፣** እዚህ በምጥ ጊዜ የሚደግፍዎን ሰዎች ይዘርዝሩ፣ እንደ አጋርዎ፣ወንድም/እህት፣ ዱውላ (በወሊድ ጊዜ የስሜት ድጋፍ የሚሰጥ ሰው)፣ ወዘተ።

**በዚህ ውልደት ላይ ያሉት ተስፋዎች፣** በዚህ ክፍል በዚህ ውልደት ላይ ያሎትን አጠቃላይ ተስፋዎች ያካቱ።

**ስለዚህ ቤት ያሎት ስጋቶች፣** እዚህ ላይ ስለ አወላለድዎ ያሎትን ስጋቶች፣ጭንቀቶች ወይም ፍርሀቶች ያካቱ።

**የህመም አመራር**

- ኤፒዱሪያል በጀርባ ታችኛው አካባቢ ያለውን የአከርካሪ ነርቭ ቦታ ለማደንዘዝ በመርፌ የሚሰጥ መድሀኒት ነው። ከሚወጋበት ቦታ ላይ እና ታች ያለውን ቦታ ያደነዝዛል እና አብዛኛውን የምጥ ህመም ይወስዳል።
- የናርኮቲክ መድሀኒት የተወሰነ የምጥ ስሜቶችን ለማደነዝ በIV (በደም ስር) ሊሰጥ ይችላል።
- በተለይም ያለ ህመም መድሀኒት ለማማጥ ከወሰኑ፣ ለተወሰነው ወይም ለሁሉም ምጥዎ፣ ተፈጥሮአዊ የምቾት እርምጃዎችን ጠቃሚ ሆኖው ሊያገኙዋቸው ይችላሉ።
- ከታች ያለው Penny Simkin Pain Management Scale (የህመም አመራር መለኪያ)። በምጥ ጊዜ የህመም አመራርን በተመለከተ ስሜትዎን ለመግለጽ ቁጥሩን መጠቀም ይችላሉ። በተጨማሪም የእንክብካቤ አቅራቢዎችዎን የህመም መድሀኒት አሁን እንደሚፈልጉ ለማሳወቅ የኮድ ቃል መምረጥ ይችላሉ።

***የህመም አመራር አማራጭ መለኪያ*** በPenny Simkin,PT (ፔኒ ሲምኪን፣ ፒቲ)የተፈጠረ። የሚከተለው በምጥ ጊዜ ህመምን መቆጣጠር ስለሚቻልበት ሊኖሩ ስለሚችሉ ስሜቶች የቁጥር መለኪያ ነው።

| **ቁጥር** | **ምን ማለት እንደሆነ** |
|---|---|
| +10 | ምንም ያለመሰማት ፍላጎት፣ ምጥ ከመጀመሩ በፊት የማደንዘዣ ፍላጎት። |
| +9 | የህመም ፍራቻ፣ እኔ ልቋቋመው እንደምችል መተማመን ማጣት፣ ለህመም ማስታገሻ በሰራተኛ ላይ ጥገኛ መሆን። |
| +7 | እርግጠኛ የማደዘንዣ ፍላጎት አቅራቢው ሊፈቅድ በሚችልበት ጊዜ ወዲያው፣ ወይም ምጥ ህመም ያለው ከመሆኑ በፊት። |
| +5 | የኤፒዱሪያል ፍላጎት ከሽግግር በፊት(7-8ሳ.ሜ)። እስከዚያው ድረስ ለመቋቋም ፍቃደኛ መሆን፣ ምናልባት በመድሀኒቶች። |
| +3 | የህመም መድሀኒት የመጠቀም ፍላጎት፣ነገር ግን በተቻለ ሁኔታ ትንሽ። ተፈጥሮአዊ የልጅ መውለድ ግብ አይደለም። |
| 0 | ምንም አስተያየት ወይም ምርጫ የለም። |
| -3 | የህመም መድሀኒት ባይኖር ይመረጣል፣ ነገር ግን ምጥ አጭር እና ቀላል ከሆነ ብቻ። |
| -5 | የህመም መድሀኒቶች እንዳይኖሩ ጠንካራ ፍላጎች ነገር ግን ለአስቸጋሪ ምጥ መቀበል። |
| -7 | በጣም ከፍተኛ የሆነ በተፈጥሮአዊ መልኩ ልጅ መውለድ፣ለራስ የግል እርካታ እንዲሁም ለህጻኑ ጥቅም። |
| -9 | በሰራተኛው መድሀኒት የመከልከል ፍላጎች፣ምንም እንኳን እራሴ ብጠይቅም |
| -10 | በቀዶ ጥገና ለሚደረግ ውልደትም መድሀኒት አልጠቀምም። |

**ምጥ እና ወሊድ**

- የልጅዎን የልብ ትርታ መቆጣጠር የሚከናወነው በምጥ ጊዜ ነው በመደበኛው ማእቀፍ ውስጥ መቆየቱን እርግጠኛ ለመሆን። እንደ እርግዝና ሁኔታዎ የሚወሰን ይህ ሊከናወን የሚችልበት የተወሰኑ አማራጮች አሉ፣
  - አልፎ አልፎ ዳመጣ (ማዳመጥ) አማራጭ ሊሆን ይችላል እርግዝናዎ እና ምጥዎ ያልተወሳሰበ ከሆነ።
  - የማያቋርጥ የኤሌክትሮኒክ የጽንስ ቁጥጥር የተወሰነ የስጋር ምክንያቶች ላልዋቸው እርግዝናዎች ይከናወናል።
  - ተንቀሳቃሽ ገመድ አልባ ቁጥጥር አልፎ ሊከናወን ይችላል ለማያቋርጥ ወይም አልፎ አልፎ ቁጥጥር እንዲንቀሳቀሱ የሚያስችሎት።

(በላይ)

- ለደምስርዎ መድሀኒት መግቢያ በመደበኛ ሁኔታ የሚደረገው ለደህንነት ነው(በተጨማሪ Hep-Lock (ሄፕሎክ) ወይም Saline Lock (ሳላይንሎክ)ተብሎ ይጠራል)። ይህ አስፈላጊ ከሆነ ከIV ፈሳሾች ጋር ሊገናኝ ይችላል።
- የተያዩ የመግፋት አቅጣጫዎች አማራጭ ሊሆኑ ይችላሉ።
- የተወሰኑ ሴቶች ህጻን ልጃቸው ሲወጣ ለማየት መስታወት መጠቀም ይፈልጉ ይሆናል።
- የተወሰኑ ሴቶች የህጻን ልጃቸውን ጭንቅላት እንደተወለደ መንካት ይፈልጉ ይሆናል።
- Pitocin (Oxytocin)ፒቶሲን (ኦክሲቶሲን) ህጻኑ እንደተወለደ በመደበኛ ሁኔታ መጠቀም ከወሊድ በኋላ ያለን መድማት ስጋት እንደሚቀንስ ተመልክቷል።
- ባብዛኛውን ጊዜ በማዋለጃ ክፍል ውስጥ አንድ የሚደግፍዎት ሰው ሊኖርዎት ይችላል። እንደ ማደንዘዣ ሰጭ ባለሞያው መልካም ፍቃድ፣ዱውላ (በወሊድ ጊዜ የስሜት ድጋፍ የሚሰጥ ሰው) አብረዎት ሊሆን ይችላል።

**ልጅዎ ከተወለደ ባኋላ**

- እኛ እንዲያጠቡ እናበረታታለን ምክንያቱም ለእርስዎ እና ለህጻን ልጅዎ ካለው በርካታ ጥቅሞች የተነሳ፣ነገር ግን ሌላ ፍላጎቶች ወይም አካላዊ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ ይህ ለእርስዎ ጥሩ አማራጭ የማይሆንበት ምክንያት። ከማጥባት ጋር ያሉ ስጋቶች ሊያካትቱ የሚችሉት የቀድሞ የጡት ቀዶ ጥገና፣የቀድሞ የማጥባት ችግር ወይም ወደውስጥ የተገለበጡ የጡት ጫፎች።
- ቫይታሚን ኬ፣የአይን ቅባት እና የሂፒታታስ ቢ ክትባት በመደበኛ ሁኔታ ለህጻን ልጅዎ የሚሰጠው መድማትን ወይም የቁስል ማመርቀዝን ለመከላከል ነው።
- እኛ እርስዎ ወይም የእርስዎ አጋር በሆስፒታል ውስጥ እያለ ህጻኑን እንዲያጥቡት እናበረታታለን። ባንዳንድ ሁኔታዎች ይህ መደረግ የሚያስፈልገው በነርስ ነው።

**የእትብት ደም**

- የዘገየ የእትብት መጣበቅ ማለት የእርስዎ የህክምና አቅራቢ የህጻኑን እትብት ለማጣበቅ ይቆያል፣ ይህ ደግሞ ብዙ ደም ከእንሽርት/ሽንት ውሀ ወደ ልጅዎ እንዲፈስ ያደርጋል።
- የልጅዎን እትብት ደም መለገስ ወይም ለግል ጥቅም ባንክ ውስጥ ለማቆየት መምረጥ ይችላሉ።
- አጋር ወይም ሌላ የድጋፍ ቡድን የህጻኑን እትብት ሊቆርጥ ይችላል።

**የህጻን ልጅ እንክብካቤ አቅራቢ**

- ለህጻን ሀኪም፣ የቤተሰብ ሀኪም፣የነርስ ባለሞያ ወይም ሌላ ለህጻንዎ የመረጡት ሌላ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ መረጃውን ይዘርዝሩ።

SWEDISH

© 2016 SWEDISH HEALTH SERVICES. ALL RIGHTS RESERVED.